

ከችግሮች ራቅ!

ሆስፒታል ሄዶ የጤና ምርመራ ቢያደርግ አስር የተለያዩ በሽታዎች ይገኙበታል ብዬ እገምታለሁ። ከነዚህ መካከል ቀላል የሚባሉት ደም ግፊትና ስኳር ናቸው። ይህ ምስኪን ሰው ከሰዎች ላይ ፍፁምነትን በመጠበቅ ራሱን ያሰቃያል። ዘወትር ከሚሰቱ ጋር ይነታረካል። ሰሃን ሰበርሽ፣ ሳሎኑን አላፀዳሽም። ልብሴን በካውያ አቃጠልሽ።

ወደ ልጆቹ ስንመጣ ኻሊድ አጥና የተባለውን ባለማጥናቱ፣ ሰዕድ አንደኛ ባለመውጣቱ፣ ሳራና ሂንድም ጥፋት በመስራታቸው ይበሳጫል። ቤት ውስጥ ሁሌም እንዲህ ነው።

ከጓደኞቹ ጋር ሲሆን ደግሞ ከዚህ የከፋ ሁኔታ ይስተዋልበታል። አቡ አብዱላህ የስስታም ሰው ታሪክ ያወራው እኔን ለመንካት ነው። ትናንት መሐመድ ስለ አሮጌ መኪና ያወራው የኔን መኪና ለማለት ነው። ምክንያቱም እኔን እያዬ ነበር የሚያወራው። የዚህ ዓይነት አስተሳሰቦች የዚህን ምስኪን ሰው አዕምሮ አጣበውታል።

"ጊዜያት ይታዘዙሃል። አለያም አንተ ትታዘዛቸዋለህ" የሚል አንድ የቆዬ አባባል አለ። አንድ ቤድዊን ጓደኛዬ ፍልስፍና ነክ ወሬዎችን ባወራሁለት ቁጥር ከአያቱ ያገኘውን ቀጣዩን አባባል ይደጋግም ነበር። በረጅሙ ይተነፍስና "ሼህ ሆይ ልታጥፈው የማትችለውን እጅ መጨበጥ አለብህ!" ይህ አባባል ትክክል ነው። ነገሮችን ችላ ካላልንና ታጋሽ ካልሆንን ወይም በሌላ አባባል ሰዎች ስለሚሉትና ስለሚያስቡት ነገር አውቀን

እንዳላወቅን ካልሆን ህይወት አስቸጋሪ ትሆንብናለች። አይችልም ሞኝ ሰው አገርን ሊመራ ሞኝ የሚመስለው ነው ይህን የሚሰራ።

አንድ ወጣት በአንድ ወቅት ወደ ኡስታዙ በመምጣት የትዳር አጋር እንዲመርጡለት ጠየቃቸው። እሳቸውም "ምን ዓይነት ሚስት ነው የምትፈልገው?" ሲሉ ጠየቁት።

"መልኳ የሚያምር፣ ቁመቷ ረጂም፣ ፀጉሯ ዘማ፣ ባለሞያ፣ ወሬዋ የሚጣፍጥ፣ ደግ፣ ታዛዥ፣ ሳያት የምታስደስተኝ፣ ራሷን ከሃራም የምትጠብቅ፣ ኃይማኖቷን የምትወድና ብልሃተኛ..." እያለ በዚያች ሴት ላይ የሚፈልጋቸውን ጥሩ ባህሪያት በሙሉ ይዘረዝር ጀመር። ሽሁ በቂ መረጃ እንዳገኙ ከተረዱ በኋላ ለወጣቱ "ልጄ ያልከውን ሁሉ የምታሟላ ሴት አለች" አሉት።

"የት?" አላቸው።

"ኢንሻ አላህ ጀነት ውስጥ። በዚህ ዓለም ላይ ግን ሙቢቃቃትን መማር ያስፈልግሃል" አሉት። አዎ! በዚህ ዓለም ላይ ቻይነትን መማር ያስፈልጋል። ችግርንና ጥልን በመፈለግ ራስህን አታሰቃይ። አንዳንዱ ከጎኑ ለተቀመጠው ሰው "ስለኔ ነው የምታወራው አይደል?" ለልጁ "በትምህርትህ የምትሰንፈው እኔን ለማበሳጨት ነው አይደል?" ለሚስቱ "ለቤቱ ትኩረት የማትሰጪው ሆን ብለሽ ነው አይደል?" ማለት ይቀናዋል። የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጠቃላይ ዘዴ ታጋሽ መሆን ነበር። በዚህ መንገድ ህይወታቸውን በደስታ መርተዋል። ጧት ወደ ቤተሰቦቻቸው ሄደው "የሚበላ ነገር አለ?" ሲሉ ይጠይቃሉ።

"የለም" ካሏቸው

"እንግዲያውስ እፆማለሁ" ይላሉ።

በዚህ የተነሳ ችግር መፍጠር አይፈልጉም። ከማንኛውም ሰው ጋር የሚቀርቡት የበዛ ታጋሽነት በመላበስ ነበር። "ምግብ ለምን አልሰራችሁም? የሚያስፈልግ ነገር ካለ ለምን አልነገራችሁኝም ገዝቼ አልመጣም ነበር ወይ" አይሉም። ይልቁንም እኔ ፆመኛ ነኝ ይላሉ። አለቀ ነገሩ። ኩልሱም ቢን አል ሁሰይብ ከድንቅ ሶሃቦች አንዱ ነበር። እንዲህ ይላል፡- "በተቡክ ውጊያ ወቅት ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ነበርኩ። በምሽት በአል አከደር ሸለቆ ውስጥ እየተጓዝን ነው። ጉዞው ረጂም ነበር። እንቅልፍ እያሸነፈኝ መጣ። ግመሌ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ግመል ትጠጋለች። ከእንቅልፌ ሰነቃ ከሳቸው አርቃታለሁ። ኮርቻው እግራቸውን እንዳይመታቸው በመፍራት።

መልሶ እንቅልፍ ሲያሸንፈኝ ግመሌ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ግመል ጋር ተጋጨችና ኮርቻው እግራቸውን መታቸው። የህመም ድምፅ አሰሙ። ይህንን ድምፅ የሰማው ኩልሱም በጣም ደንግጦ ከእንቅልፉ ነቃ።

"የአላህ መልዕክተኛ ሆይ" አላህ እንዲምረኝ ጠይቁልኝ" አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቻይነታቸውን በማንፀባረቅ "አብሽር...አብሽር..." አሉት። አዎ ይሄንን ብቻ ነው የተናገሩት። ሌላ ሰው ቢሆን ኖሮ "ምን ወደኔ ያስታከከሃል። መንገዱ ሰፊ

ነው። አቅጣጫህን ይዘህ አትሄድም እንዴ?" ይለው ነበር። እሳቸው አተካራ ውስጥ በመግባት ራሳቸውን ችግር ውስጥ አይከቱም። እግራቸው ተመታ። ነገር ግን ምንም አይደለም። ይህ ነው ዘወትር ለነገሮች የሚሰጡት ምላሽ።

ነብዩ አንዴ ከባልደረቦቻቸው ጋር ተቀምጠው እያለ አንዲት ሴት ጋቢ ይዛ በመምጣት "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ለእርስዎ ብዬ በእጄ ነው የፈተልኩት" በማለት ሰጠቻቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጣም የሚፈልጉት ነገር ነበር። ተቀበሏትና ለብሰውት ወደ ጓደኞቻቸው ሄዱ። አንድ ሰው "እባክዎትን እሱን ነገር ይስጡኝና ልልበሰው" አላቸው። ነብዩም "እሺ" አሉትና በፍጥነት ወደ ቤታቸው በመሄድ አሮጌውን ልብሳቸውን ለብሰው አዲሱን ላኩለት። አጠገቡ የነበሩ ሰዎችም "የሰራኸው ስራ ትከከል አይደለም። እሳቸው የተጠየቁትን ነገር እምቢ ማለት እንደማያውቁ እያወቅከ መጠየቅ አልነበረብህም" በማለት ሰውዬውን ወቀሱት። እሱም "ወላሂ ስሞት ለሬሳዬ መከፈኛ ላደርገው ስለፈለግኩ ነው እንጂ አልጠይቃቸውም ነበር" አለ። ሰውዬው ሲሞት ቤተሰቦቹ በዚያ ጨርቅ ከፍነው ቀበሩት። (ቡኻሪ)

አንዴ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር የኢሻን ሶላት እየሰገዱ እያለ ሁለት ህፃናት ወደ መስጊድ ገቡ። የልጃቸው ልጆች ሀሰንና ሁሴን ናቸው። ቀጥ ብለው ወደ አያታቸው ሄዱና ሱጅድ በሚያደርጉበት ጊዜ ዘለው ጀርባቸው ላይ ይወጣሉ። ቀጥ ለማለት ሲፈልጉ ቀስ አድርገው ያወርዷቸውና ከጎናቸው ያስቀምጧቸዋል። አሁንም ሱጁድ ሲያደርጉ ዘለው ጀርባቸው ላይ ይወጣሉ። ሰግደው ሲጨርሱ ሁለቱንም ቀስ አድርገው ጭናቸው ላይ አስቀመጧቸው።

አቡሁረይራ (ረ.ዐ) ተነሱና "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ልመልሳቸው?"አሏቸው። ወደ እናታቸው ላድርሳቸው ማለታቸው ነው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ግን በችኮላ እንዲመለሱ አልፈለጉም። ከኔ ጋር ይቆያሉ አሉ። ኋላ ላይ ዝናብ መጣና ብልጭታ አዩ። ሙበረቅም ሰሙ። "ወደ እናታችሁ ሂዱ" አሏቸው። ተነስተው ሄዱ። (አህመድ)

በሌላ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዙህርን ሶላት ለመስገድ ሀሰንና ሁሴንን ይዘው መስጊድ ገቡ። ልጆቹን አስቀመጧቸውና ሶላቱን ጀመሩ። ሆኖም ከተለመደው ረዘም ላለ ጊዜ ሱጁድ ላይ ቆዩ። ሶሃቦች ነብዩ የሆነ ነገር ሆነዋል ብለው እስኪያስቡ ድረስ። ሶላቱ ሲያበቃ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከወትሮው በተለዬ ሁኔታ በዚህ ሱጁድ ላይ ቆይተዋል። አላህ ያዘዘዎት ነገር አለ እንዴ? ወይስ ወህይ እየተቀበሉ ነበር" በማለት ጠየቋቸው። ነብዩም "አይደለም ልጄ ጀርባዬ ላይ ወጥቶ ነበር። እናም ቶሎ ብዬ ላወርደው አልፈለግኩም። ስለዚህ በራሱ እስኪወርድ ድረስ እየጠበቅኩት ነበር" አሉ። (ሀኪም)

አንዴ ኡሙ ሃኒ ቢንት አቡ ጧሊብን (ረ.ዐ) ለመጎብኘት ወደ ቤቷ ሄዱ። እርሷቸው ስለነበር "የሚበላ ነገር አለ?" ሲሉ ጠየቋት። እሷም "ከደረቅ ዳቦ በስተቀር ምንም የለም። እሱን ልሰጥዎት በጣም ይከብደኛል" አለች። "አምጪው" አሏት።

አመጣችውና ቆራርሳ ውሃ ወሰጥ ነከረችው። ትንሽ ጨው አምጥታም ነሰነሰችበት። ኑበዩ ይህን በውሃ የተነከረ ዳቦ መብላት ጀመሩ። "ለዳቦ ማቢያ የሚሆን ነገር አለሽ?" አሏት።

"ምንም የለኝም። ከትንሽ ኮምጣጤ በስተቀር" አለቻቸው። "አምጪው" አሏት።

አመጣችና ምግቡ ላይ አፈሰሰችበት። ኑበዩም የተወሰነውን በሉ። አላህን አመሰገኑና "ዳቦ በኮምጣጤ እንዴት ይጣፍጣል!" አሉ። አዎ! ህይወትን እንዳመጣጡ ነው የሚኖሩት። እውነታን እንዳለ ነው የሚቀበሉት።

አንዴ ከባልደረቦቻቸው ጋር ወደ ሐጅ እየተጓዙ ሳለ አንድ ቦታ ላይ አረፍ አሉና ኡዱ አድርገው ለሶላት ቆሙ። ጃቢር ቢን አብዱላህ (ረ.ዐ) መጣና አላሁ አከበር ብሎ በግራ በኩል ቆመ። ኑበዩ (ሲ.ዐ.ወ) ቀስ አድርገው በቀኛቸው በኩል አዞሩትና ሶላቱን ቀጠሉ። ጃቢር ቢን ሰኽር (ረ.ዐ) መጣ። ኡዱ አደረገና ከነበዩ (ሲ.ዐ.ወ) በግራ በኩል ቆመ። ኑበዩ (ሲ.ዐ.ወ) ሁለቱንም ትንሽ ወደ ኋላ ገፋ አደረጓቸውና አሳቸው ከፊት ሆነው ሰገዱ። (ቡኻሪ)

አንድ ቀን ኡሙ ቀይስ ቢንት መህሲን አራስ ልጇን ይዛ መጣችና ቴምር አላምጠው የህፃኑን ከንፈሮች ያስነኩለት አለቻቸው። ልጁ በረካ (ተህኒክ) እንዲያገኝና ዱዓ እንዲያደርጉለት። ኑበዩ (ሲ.ዐ.ወ) ተቀበለው አቀፉት። ብዙም ሳይቆይ ህፃኑ ሽንቱን ሸናና ልብሳቸውን አበሰበሰው። አልደነገጡም። አልተቆጡም። ያደረጉት ነገር ቢኖር ውሃ አስመጥተው ሽንት የነካው ልብስ ላይ ማፍሰስ ነበር። አለቀ ነገሩ። (ቡኻሪ)

ታዲያ እኛ ትንሽዋን ድቡልቡል አፈር ተራራ በማድረግ ለምን ራሳችንን እንጎዳለን? ባንተ ላይ የሚደርሰው ነገር ሁሉ መቶ በመቶ ካንተ ፍላጎት ጋር ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም። አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን መቆጣጠር ባለመቻል ነገሮችን ያጋንናሉ። አንዳንድ ወላጆችንና አስተማሪዎችን ጨምሮ። ድብቅ ስህተቶችን አትፈልግ። የሰዎችን ይቅርታ ለመቀበል ከፍት ሁን። በተሳይ ለግላዊ ጥቅም ሳይሆን ካንተ ጋር ያላቸውን መልካም ግንኙነት ለመጠበቅ ሲሉ ይቅርታ የሚጠይቁህን። ኑበዩን ተመልከት! አንድ ቀን ሚንበራቸው ላይ ተቀምጠው ቤታቸው ውስጥ ያሉ ሴቶች እስኪሰሟቸው ድረስ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ለሶሃቦቻቸው እንዲህ አሉ፡- ምን ያሉ ይመስልሃል?

እናንተ በምላሳችሁ ያመናችሁና እምነት ልባችሁ ውስጥ ያልገባ ሰዎች ሆይ! እባካችሁ ሙስሊሞችን አትመ። ስህተቶቻቸውን አትፈልጉ። የሰዎችን ስህተት የሚፈልግ ሰው አላህ ስህተቱን ይፈልግበታል። አላህ ስህተት የፈለገበት ሰው ደግሞ ቤቱ ውስጥ ቢደበቅ እንኳ ያጋልጠዋል! (ቲርሚዚ) አዎ ስህተትን አታፈንፍን። ጉድለትን አትፈልግ። ታጋሽ ሁን።

ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሁሌም ስህተትን ላለማገላት ይጥሩ ነበር። አንዴ ከባልደረቦቻቸው ጋር ነፍሶች የሚፀዱበት ልቦች የሚረጋጉበት ሰላማዊ ውይይት እያደረጉ ነበር። "አንዳችሁ ስለ አንዱ ባልደረባዬ መጥታችሁ መጥፎ ነገር አትንገሩኝ። ሁላችሁንም በንጹህ ልብ ልቀርባችሁ እፈልጋለሁና" አሏቸው።

ራስህን አትቅጣ...

በራስህ ላይ አቧራ አትሰብስብ። አቧራው ሲረጋጋ...

አቧራው ወደ ላይ ሲነሳ አፍንጫህን በመሀረብ ሸፍንና ህይወትህን በደስታ ኑር።



ስህተትህን ተቀበል፤ ግትር አትሁን

ሰዎችን ለዓመት፣ ለሁለት ዓመት ወይም ለእድሜ ልክ አለያይተው የሚቀሩ አንዳንድ አለመግባባቶች አንደኛው ተነስቶ "አጥፍቻለሁ ይቅርታ" ቢል በቅፅበት የሚፈቱ ናቸው።

"አዎ ያልሆነ ቀልድ ቀልጃለሁ።" "አዎ መጥፎ ነገር ተናግሪያለሁ።"

እሳቱ ከመያያዙ በፊት ለማጥፋት ፍጠን። "እባክህን ይቅርታ አድርግልኝ" በለው። ከዚያ በኋላ ሰላም ታገኛለህ። በአንድ ወቅት በቢላልና በአቡ ዘር መካከል አለመግባባት ተፈጠረ።

ምን እንኳ ድንቅ የነብዩ ባልደረቦች ቢሆኑም ሰዎች ናቸውና ተጋጩ። አቡ ዘር በጣም ተናዶ ስለነበር ቢላልን "አንተ የጥቁር ሴት ልጅ" አለው። ቢላል ለነብዩ (ሲ.ወ.ስ) ሰሞታ አቀረበ። ነብዩ አቡዘርን ጠሩትና "ቢላልን ሰደብከው?" እንዴ በማለት ጠየቁት።

"አዎ" በማለት መለሰ። "እናቱን ጠራህ?" አሉት።

እሱም "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አንድ ሰው ሲሰደብ እናትና አባቱ መነሳታቸው አይቀርም" አለ። ነብዩም "አንተ ከኢስላም በፊት የነበረው የጃሂሊያ ድንቁርና ያለቀቀህ ሰው ነህ" አሉት። "በዚህ እድሜዬ?" አላቸው።

"አዎ" አሉት።

ከዚያም እንዲህ በማለት በማህበራዊ ደረጃ ዝቅ ተደርገው የሚታዩ ሰዎችን እንዴት መቅረብ እንዳለበት አስተማሩት። "እነሱ ወንድሞችህ ናቸው። አላህ ባንተ እንከብካቤ ስር አድርጓቸዋል። አላህ እንዲንከባከበው ያስቀመጠለትን ሰው የሚበላውን ምግብ ያበላዋል። የሚለብሰውን ልብስ ያለብሰዋል። ከሚችለው በላይ ጫና አያሳድርበትም። ጫና ካለበት ደግሞ ያግዘዋል" አሉት። ከዚያስ አቡዘር ምን አደረገ? ወደ ቢላል ሄደና ይቅርታ ጠየቀው። ፊቱ አፈር እስኪነካ ድረስ መሬት ላይ

ተደፋና "ቢላል ሆይ! በእግርህ ፊቴን እርገጠኝ" አለው። (ሙስሊም)

የዚህን ያህል ነው ሶሃቦች የጥላቻ እሳት ከመቀጣጠሉ በፊት ለማጥፋት ይጓጉ የነበረው። እሳቱ ቢቀጣጠልም እንኳ ከመዛመቱ በፊት ለማጥፋት የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። አንዴ በኡመርና በአቡበከር መካከል ግጭት ተፈጠረ። አቡበከር ኡመርን አናደዷቸው። ኡመር ተበሳጭተው ወጡ። አቡበከር በሆነው ነገር ተፀፀቱ። ሁኔታው ሊባባስ ይችላል የሚል ፍራቻም አደረባቸው። ተከተሏቸውና "ኡመር ሆይ! ይቅርታ አድርግልኝ" አሏቸው። ኡመር ግን ቀጥ ብለው መንገዳቸውን ቀጠሉ። አቡበከር እየተከተሉ ይቅርታ መጠየቃቸውን ሳያቆሙ ኡመር ቤታቸው ደረሱና ገብተው በሩን ዘጉባቸው። አቡበከር ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሄዱ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አቡበከርን ሲመለከቷቸው የሆነ ነገር እንደገጠማቸው አወቁና "ይህ ጓደኛችን የሆነ ችግር የገጠመው ይመስላል" አሉ። አቡበከር ዝም ብለው ተቀመጡ።

ኡመር በሰሩት ስራ ተፀፀቱ። አላህ ሁላቸውንም ስራቸውን ይውደድላቸውና ልባቸው ምን ያህል ንጹህ እንደነበር ተመልከት። ብዙም ሳይቆይ ወደ ነብዩ ሄዱ። ሁላቸውንም ሰላም ካሉ በኋላ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጠገብ በመቀመጥ ለአቡበከር ጀርባቸውን መስጠታቸውንና ይቅርታቸውን አለመቀበላቸውን ጨምረው የተፈጠረውን ነገር ሁሉ ነገሯቸው። ነብዩ በኡመር ተቆጡ። የነብዩን መቆጣት የተመለከቱት አቡበከር "ወላሂ! የአላህ መልዕክተኛ! እኔ ነኝ ጥፋተኛው! እኔ ነኝ ጥፋተኛው!" በማለት ያስተባብሉላቸው ጀመር። ነብዩም "ባልደረባዬን ጥለኸው ሄድክ? ባልደረባዬን ጥለኸው ሄድክ? ለሁላችሁም ሰዎች ሆይ! እኔ የአላህ መልዕክተኛ ነኝ" ስላችሁ እናንተ "ዋሸህ" ስትሉኝ አቡበከር ግን እውነት ተናገርክ ይለኛል" አሉ። (ቡኻሪ)

የራሳቸውን ነፍስ እያነቀዙ የሰዎችን ስህተት ከሚያርሙ ሰዎች ከመሆን ተጠንቀቅ። የዚህ ዓይነት ሰዎች በወፍጮ ዙሪያ እየዞረ እህል እንደሚፈጭ አህያ ከስህተቶቻቸው ጋር ሲሽከረከሩ ይኖራሉ። ስለሆነም ሰዎችን በመምከር ደረጃ ላይ ካለህ ለምሳሌ አስተማሪ ከሆንክ በተማሪዎችህ፣ ባል ከሆንክ በሚስትህ፣ አባት ከሆንክ በልጆችህ ቁጥጥር ስር እንደሆንክ አስብ። እያንዳንዱ ሰው ይከታተልሃል። ስለዚህ በተቻለህ መጠን ሁሌም ስነ ስርዓት ይኑርህ።

አንዴ ኡመር (ረ.ዐ) ለሰዎች ልብሶችን አከፋፍለው ነበር። እያንዳንዱ ሰው ልኩ የሆነውን አንድ ልብስ ወሰደ። ኡመር ጁምዓ ላይ ኹጥባ ለማድረግ ተነሱ። በመጀመሪያም "በእርግጥም አላህ እንድትሰሙና እንድትተገብሩ አዟችኋል..." አሉ። ይህን ሲናገሩ አንድ ሰው ተነሳና "መስማትም መታዘዝም የለም" አለ።

"ለምን?" አሉት ኡመር።

"ለኛ የሰጠኸን አንዳንድ ልብስ ነው። አንተ ግን እንደምናይህ ሁለት አዳዲስ ልብሶችን ለብሰሃል" አላቸው።

ኡመር ከጀመሳው መካከል ሰው መፈለግ ጀመሩ። ልጃቸውን አብዱላህ ኢብኑ ኡመር። እንዳዩትም "አብዱላህ ኢብኑ ኡመር ተነስ" አሉት። ተነሳ።

"አንዱን ልብስህን አልሰጠኸኝም?" ሲሉ ጠየቁት። "አዎ!" አለ። ሰውዬውም "አሁን እንሰማለን እንታዘዛለን" በማለት ተቀመጠ። አለቀ ነገሩ።

ሰውዬው ኡመርን የሞገተበት ሁኔታ ተገቢ ባይሆንም ኡመር ሁኔታውን የተረዱበት ችሎታና የችግሩን እሳት ለማጥፋት ያደረጉት ጥረት ግን ያስደምማል። ሚስትህ፣ ልጅህ ወይም እህትህ አስተያየትህንና ምክርህን እንዲቀበሉ የምትሻ ከሆነ ትዕቢትህን ትተህ አንተም ራስህ ምክር ተቀባይ ሁን።

አንድ ሰው ለሚስቱ ዘወትር "ልጆቹን በደንብ ተንከባከቢ። ጥሩ ምግብ ስሪ። መኝታ ቤቱን እንድታስተካክይው ከነገርኩሽ ስንት ጊዜ ሆነ?" ሲላት "እሺ ኢንሻ አላህ እንዳልከው አደርጋለሁ" በማለት በብልሃት መልስ ትሰጠዋለች። አንድ ቀን ሚስቱ "ልጆች ፈተና ላይ ናቸው። አጠገባቸው ሁንና አንዳንድ ነገር አግዛቸው። ከጓደኞችህ ጋር ከሄድክም ቶሎ ብለህ ተመለስ" የሚል ምክር ትለግሰዋለች። ንግግሯን ለይስሙላ ካዳመጠ በኋላ "ለነሱ ጊዜ የለኝም። ብዘገይ ባልዘገይ ምን አገባሽ? ይህ አንቺን አይመለከትሽም" በማለት ይጮህባታል።

ለአላህ ብለህ ንገረኝ። ከዚህ ንግግር በኋላ እንዴት ብላ ነው የሱን ምክር የምትቀበለው? ብልህ ሰው ማለት ሰዎች ወደ ውስጥ አጮልቀው እንዳያዩበት ሲል የቤቱ ግድግዳ ላይ ያሉ ቀዳዳዎችን የሚደፍን ነው። ሰዎች እንዲጠራጠሩህ እድል አትስጥ። አስታውሳለሁ አንዴ አንድ የዳዕዋ ድርጅት አልባኒያ ውስጥ የዳዕዋ ሰዎችን ጋብዞ ነበር። የአልባኒያ የዳዕዋ ማዕከላት ፕሬዝዳንትም ተገኝቷል። ስናዬው አገጩ ላይ አንድ ዘለላ ፀጉር የለም። በጣም በመገረም እርስ በርሳችን ተያየን። ምክንያቱም ዳኢ በትንሹም ቢሆን ፂሙን በማሳደግ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሱና መከተል ግድ ይለዋል። እንዴት የዳዒዎች መሪ የሆነ ሰው ፂሙን ሙልጭ አድርጎ ይላጫል? ኮንፈረንሱ ሲጀመር በቀልድ እንዲህ አለን:- "ውዶች ሆይ! እኔ በተፈጥሮዬ ፂም የለኝም። ፂሜ አያድግም። ከጨረስን በኋላ በኔ ዙሪያ ትምህርት እንዳታዘጋጁ አለን" ፈገግ አልንና አመሰገነው። ከፈቀዳችሁልኝ ወደ ኋላ ወደ መዲና ልመልሳችሁ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንዴ በረመዳን ምሽት መስጊዳቸው ውስጥ ኢእቲካፍ ተቀምጠው ነበር። ሚስታቸው ሶፍያ ቢንት ሁየይ ልትዘይራቸው መጣች። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ወደ ቤቷ ለመመለስ ተነሳች። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጨለማ ብቻዋን ሊልኳት አልፈለጉም። ስለሆነም ሊሸኟት ወጡ። መንገድ ላይ አያሉ ሁለት የአንሷር ሰዎች አገኟቸው። ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ከሴት ጋር ሲያዩዋቸው ፍጥነታቸውን ጨመሩ። ይህን

የተመለከቱት ነብዩ "ተረጋጉ። እሷ ባለቤቴ ሶፍያ ቢንት ሁየይ ናት" አሏቸው። እነሱም "ሱብሃነላህ" አሉ። ነብዩን ያህል ሰው በሴት መጠርጠር ምን የሚሉት ነገር ነው?

ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "በእርግጥም ሰይጣን በሰው ልጅ ላይ የሚዘዋወረው በደም ስር ውስጥ እንዳለ ደም ነው። በልቦቻችሁ ውስጥ መጥፎ ነገር ይከታል ወይም የሆነ ነገር ሹክ ሊላችሁ ይችላል ብዬ ስለፈራሁ ነው..." አሏቸው። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ጀግንነት...

ጀግንነት በስህተት ላይ መቆየት አይደለም። መሳሳትን ማወቅና ስህተትህን አለመድገም እንጂ።